# የሰሞኑ የህዝብ መወያያዎች በጠቅላይ መኒስትሩ እይታ

አዲሰ ቶልቻ
07/25/14

የመንግስት ሰራተኞች የደሞዝ ጭማሪ ከሰሞኑ ቀልብ ሳቢ አጀንዳዎች መሃከል አንዱ ነው። የደሞዝ ጭማሪውን ቀልብ ሳቢ ያደረገው ሰራተኛው ተጨማሪ ገንዘብ ማግኘቱ ብቻ ሳይሆን፣ ጭማሪውን ተከትሎ የሸቀጦችና የአገልግሎቶች ዋጋዎች 'ጨመርኩ፣ ጨመርኩ' እያሉ ማስፈራራታቸው ነው።

የሰሞኑ ቀልብ ሳቢ አጀንዳ ይህ ብቻ አይደለም። በተለይ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአሸባሪነት የተፈረጀው ግንቦት 7 መስራችና መሪ አንዳርጋቸው ፅጌ በቁጥጥር ስር ውለው አዲስ አበባ መግባትና ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሽብርተኝነት የተጠረጠሩ የህጋዊ ፓርቲዎች አባላት በቁጥጥር ሥር መዋልም እንዲሁ መወያያ አጀንዳ ሆኖ ሰንብቷል።

ታዲያ በየወቅቱ በአገራዊ ጉዳዮች ላይ ለጋዜጠኞች ማብራሪያ ሰሰጡ የቆዩት የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ሰሞኑን በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ እነዚህን በሕዝቡ ዘንድ መወያያ የሆኑ ጉዳዮችን የተመለከቱ እና ሌሎችም ጥያቄዎች ቀርበውላቸው ማብራሪያ ሰጥተውበታል። እኔም በዚህ ፅሁፍ በተለይ ከላይ የተገለፁት ሁለት ጉዳዮችን በተመለከተ ጠ/ሚር ኃ/ማሪያም የሰጡትን ማብራሪያ ከነባራዊው ሁኔታ ጋር አዛምጄ ልቃኛቸው ወድጃለሁ።

### የደሞዝ ማሻሻያና የዋጋ ንረት

በፌዴራልና በክልል መንግስታት ውስጥ በአጠቃላይ በመንግስት ስራ ላይ የተሰማሩት ዜጎች ቁጥር 1 ነጥብ 3 ሚሊዮን ገደማ መሆኑ ይታወቃል። የመንግስት ሰራተኞች እንደሌሎች ቁርጥ ደሞዝ ተከፋዮች የገንዘብ ግሽበት ወይም የዋጋ ንረት በሚኖርበት ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ተጎጂዎች ናቸው። ከመንግስት ሰራተኛ ውጭ ያሉ ቁርጥ ደሞዝ ተከፋዮች የመንግስት የልማት ድርጅት ሰራተኞችን ጨምሮ የደሞዝ ደረጃቸውና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታው የሚፈጥረውን ጫና ተከትሎ የሚደረግ የደሞዝ ማስተካከያ በካምፓኒ

አስተዳደር የሚወሰን ነው። በዚህ መሰረት ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ መንግስታዊና የግል ኩባንያዎች በተለያየ ጊዜ የደሞዝ ማስተካከያ ሲያደርጉ ቆይተዋል። በእነዚህ የግልና መንግስታዊ የልማት ድርጅቶች የሚከናወን የደሞዝ ማስተካከያ በተለያየ ጊዜ በኩባንያ ደረጃ የሚወሰን በመሆኑ ጭማሪው ትኩረት የሚስብ ዜና አይሆንም።

የመንግስት ሰራተኞች በአንድ የመተዳደሪያ ደንብ የሚተዳደሩና ደሞዛቸውም ከአንድ ቋት (ከመንግስት በጀት) የሚቀዳ በመሆኑ፣ የደሞዝ ማስተካከያው በምኒስትሮች ምክር ቤት የመንግስት የስልጣን ደረጃ  የሚፀድቅ በመሆኑ ትልቅ ዜና ይሆናል። ልብ በሉ የመንግስት ሠራተኞች የደሞዝ ማስተካከያ ተጠቃሚ የሚያደርጋቸው ዜጎች ቁጥርና ወደ ኢኮኖሚው ውስጥ የሚገባው ገንዘብ ከፍተኛ ስለሆነ አይደለም ዜና የሚሆነው። ጭማሪው ለሁሉም የመንግስት መስሪያ ቤት ሰራተኞች በአንድ ጊዜ በአዋጅ የሚከናወን ነው።

ይህ ሁኔታ ከዚህ ቀደም በተደረጉ የመንግስት ሠራተኞች የደሞዝ ማስተካከያዎች እንዳየነው ተጨባጭ ኢኮኖሚያዊ ባልሆነ ምክንያት የሸቀጦችና የአገልግሎቶች ዋጋ እንዲጨምር ምክንያት ይሆናል። በ1999 ማብቂያ ላይ እንዲሁም በ2003 ዓ/ም በተደረገው የመንግስት ሰራተኞች የደሞዝ ማስተካከያ ላይ ይህ ሁኔታ አጋጥሟል።

በመሆኑም ሰራተኛው በደሞዝ ጭማሪ አገኘዋለሁ ብሎ ጠብቆ የነበረውን ጥቅም በተወሰነ ደረጃ ሳያገኝ ቀርቷል። በእነዚህ ወቅቶች የነበረው ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ያስከተለው የገንዘብ ግሽበት ለዚህ አስተዋፅኦ የነበረው መሆኑ ሳይዘነጋ፣ ኢኮኖሚያዊ ገፊ ሁኔታ የግድ ካለው ውጭ ነጋዴዎች በስምምነት ያደረጉት የዋጋ ጭማሪም የመንግስት ሰራተኛው ከደሞዝ ጭማሪው የሚገባውን ጥቅም እንዳያገኝ በማድረግ ረገድ የቀላል የማይባል ድርሻ ነበረው።

በ2003 ዓ/ም ሊፈጠር ይችል የነበረውን የዋጋ ንረት ለመከላከል መንግስት እርምጃዎች ወስዶ ነበር። ከእነዚህ መሃከል መሰረታዊ የፍጆታ ምርቶች የሆኑት የምግብ ዘይት፣ የስኳርና የስንዴ - ዳቦ ስርጭትና የመሸጫ ዋጋ በመንግስት ቁጥጥር ስር እንዲውል መደረጉ ተጠቃሽ ነው። ይህ እርምጃ በመንግስት ሰራተኛ ላይ በዋጋ ጭማሪ ሊፈጠር ይችል የነበረውን የከፋ ጫና ትርጉም ባለው መጠን አቃሎታል ማለት ይቻላል።

አሁን ከያዝነው ወር ማለትም ከሃምሌ 2006 ዓ/ም ጀምሮ እንዲደረግ የተወሰነው የመንግስት ሰራተኞች የደሞዝ ማስተካከያ እርምጃም "ተገቢ ያልሆነ የዋጋ ንረት ይፈጥራል" የሚል ስጋት አሳድሯል። ገና የደሞዝ ጭማሪው ተግባራዊ ሳይደረግ በአንዳንድ ምርቶች ላይ ጉልህ ጭማሪዎች መታየት መጀመራቸው ደግሞ ስጋቱን አጠናክሮታል። እንግዲህ የሰሞኑ የደሞዝ ጭማሪ መወያያ ጉዳይ ለመሆን የበቃው፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ማብራሪያ እንዲሰጡበት የግድ ያለው በዚህ ምክንያት ነው።

ታዲያ ከዚህ የመንግስት ሰራተኞች የደሞዝ ጭማሪ ጋር ተያይዞ አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች "መንግስት ጭማሪውን ያደረገው በቀጣዩ አመት ለሚካሄደው ምርጫ ብሎ ነው።" ሲሉም ተደምጠዋል። "ጭማሪውን አስፈላጊ የሚያደርገው ምንም ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ የለም።" ማለታቸው ነው። "የደሞዝ ማስተካከያው ግሽበት ማስከተሉ አይቀሬ ነው" ብለው ውዥንብር በመፍጠር የዋጋ ንረቱ ኢኮኖሚያዊ ባልሆነ ሁኔታ እንዲፈጠር መንገድ የጠረጉ የምጣኔ ሃብት ባለሙያዎች ነን ያሉ ሰዎችና የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች አመራሮችንም አድምጠናል።

በዚህ ውዥንብርና በሌሎችም ምክንያት በአንዳንድ ምርት ላይ የዋጋ ጭማሪ ታይቷል። ይህ የዋጋ ጭማሪ የፈጠረውን ስጋትና በዚህ ከቀጠለ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ከግምት በማስገባት በመንግስት በኩል ማሳሰቢያዎች እየተሰጡ ነው። ማሳሰቢያዎቹ ሸማቹ ሊፈጠር የሚችለውን ሰው ሰራሽ የዋጋ ጭማሪ ለመከላከል በሸማቾች የህብረት ሥራ ማህበራት እንዲደራጅና ማህበራቱን እንዲጠቀም እንዲሁም ተገቢ ያልሆነ የዋጋ ጭማሪ የሚያደርጉት ላይ ሕጋዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚደረገው ሥራ ላይ ትብብር እንዲያደርግ የሚጠይቁ ናቸው።

ያም ሆነ ይህ የዋጋ ጭማሪው መታየት ጀምሯል፤ በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ። ይህን ተከትሎ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድና ኢንደስትሪ ልማት ቢሮ እርምጃዎችን ወስዷል። በዚሁ መሰረት ከባለፈው ሳምንት አርብ ማለትም ሃምሌ 11 ጀምሮ በህብረተሰቡ ጥቆማና በንግድ ቢሮዎች ቁጥጥርና ክትትል አማካኝነት ኢኮኖሚያዊ ምክንያት የሌለው የዋጋ ጭማሪ ያደረጉ 248 ነጋዴዎች ሱቆች መታሸጋቸውን ቢሮው አስታውቋል።

እንግዲህ፣ ‘መጣሁ፣ መጣሁ’ እያለ ስጋት ለፈጠረው ዋጋ ንረትና ለመንግስት ሰራተኞች የደሞዝ ጭማሪ ማድረጉን አስፈላጊ ያደረገውን ሁኔታ አስመልክቶ ጠቅላይ ምኒስትር ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ባለፈው አርብ ከጋዜጠኞች የቀረበላቸውን ጥያቄ መነሻ በማደረግ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ሰጥተዋል።

ጠቅላይ ምኒስትር ኃ/ማርያም በዚህ ዙሪያ በሰጡት ማብራሪያ፣ “የደሞዝ ማስተካከያውን ተከትሎ በአንዳንድ ሸቀጦች ላይ የዋጋ ጭማሪ ታይቷል።” ብለዋል። በማያያዝም የደሞዘ ማስተካከያ ማድረግ ያስፈለገበትን ምክንያት ሲገልፁ፣ በ2003 ዓ/ም የተደረገውን የደሞዝ ማስተካከያ አስታውሰው፣ “ከዚህ በኋላ ባሉት አመታት እስከ 40 በመቶ የደረሰ የገንዘብ ግሽበት ተከስቶ ነበር” ብለዋል። ይህን ተከትሎ የገንዘብ ግሽበቱን ለማረጋጋት መንግስት የገንዘብና የፊሲካል ፖሊሲ ማስተካከያዎችን እንዲሁም ዋጋን የሚያረጋጋ አስተዳደራዊ እርምጃ በመውሰዱ ላለፉት ሁለት አመታት (2005 እና 2006) የገንዘብ ግሽበቱን በአንድ አሃዝ ደረጃ መያዝ መቻሉን የተናገሩት ጠቅላይ ምኒስትር ኃ/ማሪያም፣ ሆኖም በግሽበቱ ምክንያት የተፈጠረውን የሸቀጦችና የአገልግሎቶች ዋጋ ከግሽበቱ በፊት ወደነበረበት መመለስ የማይቻል መሆኑን ገልፀዋል። ይህ በአንድ አሃዝ የተገደበ ግሽበት ትክክልና ተገቢ መሆኑንም አስታውቀዋል።

ይሁን እንጂ የዋጋ ግሽበቱን በአንድ አሃዝ መገደብ መቻሉ ቋሚ ገቢ ያላቸው የሕብረተሰብ ክፍሎችን ጉዳት መቀነስ እንደማይቻል ነው ጠቅላይ ምኒስትር ኃ/ማርያም የተናገሩት። በመሆኑም አነስተኛ ገቢ ያላቸውን የሕብረተሰብ ክፍሎች ገቢያቸው እንዲያድግ ማድረግ የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን ተግባራዊ ማድረግ፣ የስራ ዕድል መፍጠር፣ በደሞዝ የሚተዳደሩ የሕብረተሰብ ክፍሎችንም እንደዚሁ የሚያስተዳድራቸው ወይም የሚያገለግሉት አካል በየጊዜው ማስተካከያዎችን እያደረገ ጉዳቱን መቀነስ እንደሚጠበቅ ገልፀዋል። አያይዘውም፣ በዚሁ መሰረት የመንግስት ሰራተኞችን ደሞዝ ማስተካከል አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱን ገልፀዋል።

ጠቅላይ ምኒስትር እንዳሉት፣ በ2003 ዓ/ም የደሞዝ ጭማሪ ከተደረገ በኋላ የዋጋ ንረቱ እየጨመረ መጥቶ በተለይ በ2004 አጋማሽ ገደማ እስከ 40 በመቶ ደርሶ ነበር። ከዚያ በኋላ በተወሰዱ ግሽበትን የመቆጣጠሪያ እርምጃዎች የግሽበቱ መጠን አንድ ኢኮኖሚ

ውስጥ ሊኖር ወደሚገባው ጤናማ መጠን- ወደ አንድ አሃዝ ወርዷል። አሁን የሸቀጦችና የአገልግሎቶች ዋጋ የሚጨምረው ከሁለት አመት በፊት በነበረበት 30 እና 40 በመቶ ሳይሆን በአንድ አሃዝ ነው። ብሄራዊ የስታስቲክስ ኤጀንሲ በያዝነው ወር እንዳስታወቀው የሰኔ ወር የግሽበት መጠን 8 ነጥብ 5 በመቶ ነው። ግንቦት ወር ላይ 8 ነጥብ 7 በመቶ ነበር። ግሽበቱ በዚሁ ተገቢ በሆነው ደረጃ ውስጥ መጠነኛ ማዘቅዘቅ አሳይቷል ማለት ነው።

ከ30 እና ከ40 በመቶ ደርሶ የነበረውን ሽምጣጭ ግሽበት (galloping inflation) ገትቶ ተገቢ የሆነ አነስተኛ ደረጃ ላይ ማድረስ ቢቻልም፣ ይህ ማለት በአጠቃላይ የሸቀጦችና የአገልግሎቶች ዋጋ ግን ግሽበቱ ከመጀመሩ በፊት ማለትም በ2003 ወደነበረበት ደረጃ ተመለሰ ማለት አይደለም። ግሽበቱን በመቆጣጠር የተቻለው ዋጋውን ወደኋላ መመለስ ሳይሆን ከነበረበት እንዳይሸመጥጥ ማደረግ ነው።

በዚህ ሁኔታ ግሽበቱ ጣሪያ ነክቶ ከነበረበት ጊዜ በፊት ያገኙት የነበረው ገቢያቸው ያልጨመረ ዜጎች አሉ፤ ቁርጥ ደሞዝ ተከፋዮች። ከነዚህ መሃከል የመንግስት ሰራተኞች ተጠቃሾቹ ናቸው። የመንግስት ሰራተኛው በ2003 የደሞዝ ማሻሻያ ከተደረገ በኋላ በተፈጠረው ግሽበት አሁን መጀመሪያው ይኖር የነበረውን ያህል መኖር የማይችልበት ሁኔታ ተፈጥሯል። በመሆኑም የመንግስት ሠራተኛውን ኑሮ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታው የግድ ካለው ሁኔታ ጋር ለማስተካከል የደሞዝ ጭማሪ ማድረግ የግድ አስፈላጊ ነው። የመንግስት ሠራተኛው አሰሪና አስተዳዳሪ መንግስት በመሆኑ ማስተካከያውን የሚያደርገው መንግስት ነው።

እዚህ ላይ፣ የደሞዝ ማስተካከያው የተደረገው የገንዘብ ግሽበቱ በአንድ አሃዝ ደረጃ ተገድቦና ግሽበት ሊፈጥሩ የሚችሉ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች በመሉ በቁጥጥር ስር ውለው ቢሆንም፣ ቀደም ሲል  እንደጠቀስኩት ጠቅላይሚኒሩም እንዳረጋገጡት በአንዳንድ ሸቀጦች ላይ የዋጋ ጭማሪ እየታየ ነው።

ጠቅላይ ምኒስትር ኃ/ማርያም በሰሞኑ ጋዜጣዊ መግለጫቸው በዚህ ዙሪያም ማብራሪያ ሰጥተዋል። በሰጡት ማብራሪያ፣ "የደሞዝ ማስተካከያው በሚደረግበት ጊዜ የዋጋ ግሽበት

መቆጣጠር ብቻ ሳይሆን፣ የዋጋ ግሽበቱ ተመልሶ ሊቀሰቀስ መቻል አለመቻሉ መረጋገጥ ነበረበት። ከዚህ አንፃር የመንግስት ሰራተኞች ደሞዝ በመንግስት አመታዊ በጀት ውስጥ የሚካተት እንደመሆኑ መጠን የአመታዊ በጀቱ ጉድለት ለዋጋ ግሽበት የሚያጋልጥ ነው አይደለም የሚለው ይፈተሻል። ከዚህ አንፃር የ2007 በጀት የዋጋ ግሽበት የማይቀሰቅስ መሆኑ በአግባቡ ተፈትሿል። ብለዋል። አንደኛው የባጀት ጉድለቱ ምጣኔ በራሱ የዋጋ ግሽበት የማይቀሰቅስ መሆኑ ተረጋግጧል። ሁለተኛ መንግስት ይህን ጉድለት የሚሸፍንበት መንገድም ቢሆን ሙሉ በሙሉ ከብሄራዊ ከሚያገኘው ብድር ብቻ ሳይሆን በሌሎች ምንጮችም ጭምር በገበያ ውስጥ ወይም በአገሪቱ ከሚዘዋወረው ገንዘብ ጭምር እንዲሆን ተወስኗል። ስለዚህ ከጉድለቱ ውስጥ ግማሹ የሚሆነው ከብሄራዊ ባንክ ብድር የምናገኘው ባለመሆኑ በእነዚህ ምክንያቶች የመንግስት ሰራተኞች የደሞዝ ማስተካከያ በምንም መልኩ የዋጋ ግሽበት ሊቀሰቅስ የሚችል እንዳልሆነ ተረጋግጧል።” ብለዋል።

ጠቅላይ ምኒስትር ኃ/ማርያም እንደገለፁት ቀደም ባሉት አመታት ተቀስቅሶ የነበረውን አይነት የገንዘብ ግሽበት ሊቀሰቅስ የሚችል ሁኔታ አለመኖሩ ከተረጋገጠ በኋላ ነው የደሞዝ ማሰተካከያው የተደረገው። የገንዘብ ግሽበት ከሚፈጥሩ ምክንያቶች አንዱ በተጨባጭ ገበያ ላይ ያለ ምርትና አገልግሎትን የማይወክል ገንዘብ ወደኢኮኖሚው ውስጥ እንዲገባ ማድረግ ነው። በዚህ ረገድ ለ2007 የተያዘው አጠቃላይ የአገሪቱ በጀት በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውጭ በሆነ ተጨማሪ ገንዘብ እንዲሸፈን የግድ የሚል ሰፊ ጉድለት የለበትም። ጉድለቱ የዋጋ ግሽበት አያስከትልም ተብሎ ከሚገመተው የ3 በመቶ በታች ነው። ይህም የአጠቃላይ የሃገሪቱ አመታዊ ምርት (GDP) 1 ነጥብ 6 በመቶ ብቻ ነው።

የመንግስት ሰራተኛው የደሞዝ ጭማሪም በዚህ ግሽበት ሊያስከትል የሚችል ጉድለት በሌለበት በጀት ውስጥ የተካተተ ነው። ስለዚህ የደሞዝ ጭማሪውን ለማድረግ የሚፈልገው ተጨማሪ ገንዘብ ግሽበት ሊያስከትል አይችልም። ከዚህ በተጨማሪ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደነገሩን ይህ እጅግ አነስተኛ የሆነና ግሽበት የማስከተል አቅም የሌለው ጉድለትም ቢሆን ሙሉ በሙሉ ከብሄራዊ ባንክ በሚገኝ ተጨማሪ ገንዘብ የሚሸፈን ሳይሆን፣ የግምጃ ቤት ሰነድ ሽያጭን በመሰለ ኢኮኖሚ ውስጥ ያለን ገንዘብ በመበደር የሚሸፈን ነው። በመሆኑም የደሞዝ ጭማሪው ገንዘብ እንዲጋሽብ በማድረግ የዋጋ ንረት ሊፈጥር የሚችልበት አንዳችም ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ የለም።

ይሁን እንጂ የዋጋ ጭማሪ "መጣሁ መጣሁ" እያለ ነው። ጠቅላይ ምኒስትር ኃ/ማርያም በዚሁ ዙሪያ ያለውን እውነታ አስመልክቶ "አሁን የሚታየው የዋጋ ጭማሪ የመንግስት ሰራተኛው ደሞዝ ገና ባልተከፈለበት ሁኔታና ይህ ገንዘብ ወደኢኮኖሚው ባልተንቀሳቀሰበት ሁኔታ የተፈጠረ በመሆኑ ምንም አይነት ኢኮኖሚያዊ ምክንያት የሌለው መሆኑን ማየት ይቻላል።"ብለዋል።

ከዚህ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ማብራሪያ መረዳት የምንችለው የደሞዝ ጭማሪው ገና በክፍያ ደረጃ ባለመፈፀሙ ጭማሪው የሚፈጥረው ገንዘብ ገና ወደኢኮኖሚ ውስጥ አልገባም።እናም ሆነ ተብሎ የተደረገ ወይም ሁኔታዎችን በአግባቡ ካለመረዳት መጪውን የገበያ ሁኔታ አዛብቶ በመተርጎም የተፈጠረ ነው።

እርግጥ አንዳንድ የምጣኔ ሃብት ባለሙያ ነን የሚሉ ሰዎችና የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች በሚነዙት "በደሞዝ ማሻሻያው ምክንያት የዋጋ ንረት መፈጠሩ አይቀሬ ነው" የሚል አስረጂ የሌለው ወሬ ሸማቾች ተደናግጠው በተወሰነ ወቅት ከሚፈልጉት በላይ ሸመታ እንዲያካሂዱ በመገፋት በተጨባጭ የሌለ ከፍተኛ ፍላጎት ፈጥሮ ዋጋ ላይ ተፅእኖ አሳድሮ ሊሆን ይችላል። ነጋዴውም የደሞዝ ጭማሪው ተግባራዊ ሲሆን "አይቀሬ" ከሆነው የዋጋ ጭማሪ ለመጠቀም ሸቀጦችን ከገበያ ዝውውር ውጭ በማድረግ በተጨባጭ የሌለ እጥረት ፈጥሮ ዋጋ ላይ ተፅእኖ ያሳደረበት ሁኔታ ሊኖረ ይችላል።

ይህ በተጨባጭ የሌለ ከፍተኛ ፍላጎት እና/ወይም በተጨባጭ የሌለ አቅርቦት የሚፈጥሩት የዋጋ ንረት ሰው ሰራሽና ተገቢ ባለመሆኑ ባለሙያ ነን ባዮቹና ፖለቲከኞቹ ውዥንብር መንዛታቸውን ቢተዉ መልካም ነው።

## የሽብርተኝነትን መረብ መበጣጠስ

ጠቅላይ ሚኒስትር ኃ/ማርያም በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ምላሽ የሰጡበትና የህዝቡንም ትኩረት ስቦ የነበረው ሌላው ጉዳይ፣ በተለይ ከግንቦት 7ቱ መስራችና መሪ አንዳርጋቸው

ፅጌ ጋር በተያያዘ ሽብርተኝነትን በመከላከል ረገድ እየተወሰደ ያለውን እርምጃ የሚመለከት ነው።

የአንዳርጋቸው ፅጌን በቁጥጥር ስር መዋል በአጠቃላይ ኢትዮጵያ እያካሄደችው ከሚገኘው የፀረሽብር ትግል ጋር በማያያዝ ነበር ጠቅላይ ምኒስትሩ ማብራሪያ የሰጡት፡፡ በዚህ ጉዳይ ዙሪያ በሰጡት ማብራሪያ “ይህ ግለሰብ በሽብር ተግባር ውስጥ የተሰማራ ብቻ ሳይሆን፣ የሽብር ተግባርን የሚያቀናጅ ዋነኛ ተዋናይ የሆነና ባለፉት አምስት አመታት ከሸአቢያ ጋር መሽጎ አገራችንን ለማተራመስ ከፍተኛ ሙከራ ሲያደርግ የቆየ ሰው ነው። ይሄ ሰው ዛሬ ብቻ ሳይሆን ከዛሬ በፊት በዚሁ ተግባሩ እርሱ የላካቸው አሸባሪዎችና ኢትዮጵያን በተለይም ደግሞ አዲስ አበባን ለማሸበር ባደረጉት ሙከራ መንግስት እጅ ከፍንጅ በቁጥጥር ሥር አውሎ በሕግ እንዲቀጡ አድርጓል። ስለዚህ የዚህን አሸባሪ ጉዳይ በተመለከተ መንግስት ከዛሬ አምስት ወይም አራት አመት ጀምሮ እስከአሁን ድረስ ተላልፎ እንዲሰጥ ለማደረግ የሚመለከታቸውን መንግስታት ጥያቄ ሲያቀርብ ነው የቆየው። ስለዚህ የዚህ አሸባሪ ጉዳይ አዲስ አይደለም።” ብለዋል። አንዳርጋቸው ፅጌ አሁን ወዳጅ አገር በሆነችው የየመን መንግስት ተላልፎ መሰጠቱንም አስታውሰዋል።

እንግዲህ ጠቅላይ ምኒስትረ ኃ/ማርያም  እንደገለጹት፣ እንዳርጋቸው ፅጌ ኢትዮጵያ ላይ የሽብር ጥቃት ለመፈፀም ከኤርትራ መንግስት ጋር ሲንቀሳቀስ ነበር። ጠቅላይ ምኒስትሩ “የአንዳርጋቸው ፅጌ መያዝ በሽብርተኞች ካምፕ ላይ የሚያመጣው ተፅእኖ ቀላል አይደለም።” የሚል እምነት እንዳላቸው በሰጡት ማብራሪያ አመልክተዋል። አያይዘውም፣ “ከዛ ባሻገር እነዚህ አሸባሪዎች ለብቻቸው ትርጉም አላቸው ወይ?” የሚል ጥያቄ አንስተው በሰጡት ማብራሪያ “እነዚህ አሸባሪዎች የተደገፏቸው መንግስታት አሉ። በእነዚሀ ላይ ትኩረተ የምናደረገው የኢትዮጵያን ሉዓላዊነተ፣ የኢትዮጵያን ሰላምና እድገት፣ ለማናጋት በሚፈልጉ መንግስታት ውስጥ የተጠለሉ መሆናቸው በግል ከሚያደርጉት ተፅእኖ በላይ ተፅእኖ ለማሳረፍ የሚያስችል አቅም ስላላቸው ነው። ይሄ አሸባሪ (አንዳርጋቸው ፅጌ) ለብቻው ግንቦት 7 የተባለውን ድርጅት ብቻ ይዞ ኢትዮጲያ ላይ የሚያደረገው ነገር በጣም ከፍተኛ ነው ከሚል ሥጋት አይደለም። ይህ አሸባሪና ቡድኖቹ የሚተማመኑባቸውና እንደተሸካሚ ፈረስ የሚጋልቧቸው መንግስታት አሉ።” ብለው፣ ዋናው የፀረሽብርተኝነት

ትግል በተለይ ግንቦት 7 በተጠለለበት የኤርትራ መንግስት የተዘረጋውን የሽብር መረብ መበጣጠስ መሆኑን አስታውቀዋል።

ከዚህ ቀደም የጋምቤላ ነፃነት ንቅናቄ ብሎ ራሱን የሚጠራ አሸባሪ ቡድን ዋና መሪ፣ እንዲሁም የኦብነግ ዋነኛ መሪዎችን በቁጥጥር ሥር በማዋል የሽብር መረባቸውን የመበጣጠሰ እርምጃ መወሰዱን ያስታወሱት ጠቅላይ ምኒስትር ኃ/ማርያም፣ ይህም መንግስት መነሻውን አስመራ አድርጎ በተለያዩ አቅጣጫዎች ኢትዮጵያን ለማተራመስ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ እየተከታተለ የሚበጣጥስ መሆኑን ማሳያ እንደሆነ አስረድተዋል። የአንዳርጋቸው ፅጌ መያዝም የመረቡን መበጣጠስ የሚያሳይ መሆኑን ገልፀዋል። በዚህ መረብ ውስጥ ንክኪና ትብብር ያላቸው ሕጋዊ የፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ የተሸሸጉ፣ የመረቡ ጫፎች ስለሆኑ የሚያዙበት ሁኔታ መፈጠሩንም ጠቁመዋል። ይህ የአንዳርጋቸው ፅጌን በቁጥጥር ስር መዋል ተከትሎ በሽብር ወንጀል ተጠርጥረው የተያዙትን የህጋዊ ፖለቲካ ፓርቲዎች አባላት የሚመለከት ነው።